የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፱
አዲስ አበባ ነሀሴ ፲፪ ቀን ፪ሺ፱

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.69
ADDIS ABABA 18th August, 2017

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፰ /፪ሺ፱ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሞዛምቢክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ..........................................ገጽ ፱ሺ፯፻፴፯

**CONTENTS**

Proclamation No.1038 /2017

Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Mozambique for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation…………… ……………..… page 9737

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፰ /፪ሺ፱

**በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብር ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈጸምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሞዛምቢክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሞዛምቢክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈጸምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## Proclamation No.1038/2017

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF MOZAMBIQUE FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME.**

**WHEREAS**, an Agreement for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income (the Agreement) was signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Government of the Republic of Mozambique on the 15th day of February 2017, in Addis Ababa;

**WHEREAS** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 29th day of June 2017;

**NOW,THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሞዛምቢክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፰/፪ሺ፱ ”ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.የስምምነቱ መጽደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሞዛምቢክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈጸምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫.የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡

**፬.አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሀሴ ፲፪ ቀን /፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1.Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Mozambique for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No .1038 /2017 .

**2.Ratification of the Agreement**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Mozambique for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed on the 15th day of February 2017 is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

Ministry of Finance and EconomicCooperation is hereby empowered to implement the Agreement in cooperation with the concerned government organs.

**4.Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on the 18th day of August 2017**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**